QuickNotes mcps

**አዲሱ የወላጅ አካዴሚ ዎርክሾፖች ፕሮግራም**

**የ**MCPS **የወላጅ አካዴሚ ለወላጆችና ለማህበረሰቡ አባላት በት/ቤት የልጆቻቸውን ስኬት ለመደገፍ መረጃዎች፣ መገልገያዎች፣ መሳርያዎችና ምክሮች ያበረክታል።**

**የዊንተር ዎርክሾፕ ወራት ሰኞ ጃንዩ.** 13 **ይጀምራል። ስለ ኮሌጅና ስራ ፕላን ዝግጅት፣ የአሳዳጊነት ስልቶች፣ እና ኮምፒውተር ደህንነት** (cybersafety) **እና ማህበራዊ ደህንነት፣ እና የተለያዩ ተጨማሪ ርእሶች አያምልጧችሁ።**

**የወላጅ አካዴሚ ዎርክሾፖች ነፃ ናቸው። የልጆች እንክብካቤና የትርጉም አገልግሎቶች በሁሉም ስብሰባዎች ይቀርባሉ። የኮርሶች የተሟላ ዝርዝር በ[ወላጅ አካዴሚ ድር ጣብያ ይገኛል]።**

**ከ**College Goal Sunday (**የኮሌጅ ግብ እሁድ**) **ጋር የፋይናንስ እርዳታን ማትረፍ**

**ስለኮሌጅና እንዴት እንደሚከፈል ማሰብ ጀምረው እንደሆነ፣ ስለ የ**2014 College Goal Sunday (**የኮሌጅ ግብ እሁድ**) **እሁድ ፌብሩ.** 9 **እና ሃሙስ ፌብሩ.** 27 **በ**Montgomery College **በሚካሄዱ ክውነቶች ይማሩ። የ**College Goal Sunday **ቀኖችና ቦታዎች የሚከተሉት ናቸው፡**

**ፌብሩ.** 9፣ 2-4 p.m. (**የበረዶ ቀን፣- ፌብሩ.** 16)
Montgomery **ኮሌጅ ታኮማ ፓርክ/ሲልቨር ስፕሪንግ ካምፓስ**
7625 Fenton Street, Takoma Park, Charlene R. Nunley Student Services Center

**ፌብሩ.** 27፣ 4-6 p.m. (**የበረዶ ቀን፡- ማርች** 6)
Montgomery **ኮሌጅ ጀርማንታውን ካምፓስ**
20200 Observation Drive, Germantown, High Technology and Science Center (HT Building)

**ለተጨማሪ መረጃዎች** [College Goal Maryland **ድር ጣባያ**] **ይጎብኙ።**

ከSuperintendent Starr ጋር የሚመጡ ክውነቶች

Superintendent Joshua Starr በሚመጡት በርካታ ወሮች በርካታ የህዝብ ግንኙነት ክውነቶች ያካሂዳል። እነዚህ ክውነቶች—የማህበረሰብ እለቶችና የተማሪ Town Halls የሚያካትቱ—የMCPS ማህበረሰብ ጥያቄዎች ለማቅረብና ሀሳቦቻቸውን ለማጋራት እድል ይሰጣሉ።

***የማህበረሰብ ቀኖች***

**የትምህርት አመቱ ሶስተኛ የማህበረሰብ ቀን የተመደበው ለሰኞ፣ ፌብሩ. 3 ሲሆን** የBethesda-Chevy Chase፣ Winston Churchill፣ Richard Montgomery፣ Rockville፣ Walter Johnson፣ Walt Whitman ት/ቤቶች እና የThomas S. Wootton ክላስተሮችን ያካትታል። Dr. Starr ት/ቤቶችን በመጎብኘት፣ ከሰራተኞች ጋር በመገናኘት፣ እና ከወላጆች መሪዎች ጋር በመነጋገር ቀኑን ያሳልፈዋል። ዕለቱ የሚጠቃለለው ወላጆች እና ሌሎች የማህበረሰብ አባላት Dr. Starrን ጥየቄ በሚያቀርቡበት በWinston Churchill High School የTown Hall ስብሰባ በ7:30 p.m. ነው።

**የትምህርት አመቱ የመጨርሻ የማህበረሰብ ቀን የሚከናወነው ሰኞ ኤፕረ 28 ሲሆን** የሚያጠቃልለውም፡- James Hubert Blake፣ Paint Branch እና Springbrook (Northeast ክንሰርሽም)፣ Col. Zadok Magruder እና Sherwood ክላስተሮች. Town Hall ስብሰባ የሚከናወነው በPaint Branch High School ነው።

***የተማሪ ታውን ሆሎች***

Superintendent Starr ሶስተኛውን የተማሪ Town Hall ስብሰባ **ማክሰኞ፣ ጃንዩ. 28፣** በNorthwood High School ነው። Dr. Starr በአዳራሹ ከተገኙ ተማሪዎች እና እንዲሁም በኢሜይልና በትዊተር ለሚቀርቡ የተወሰኑ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል።

የቀሪዎቹ የተማሪ Town Halls ቀኖችና ቦታዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

**ሀሙስ ፌብሩ. 27፣** Rosa Parks Middle School
**ማክሰኞ፣ ማርች 18፣** Watkins Mill High School
**ሀሙስ፣ ኤፕረል 24፣** Herbert Hoover Middle

ካለፉት Town Hall ክውነቶች ቪድዮዎች ለማየት የተማሪ Town Hall ድረገፅ ይጎብኙ።

**በቅርብ ጊዜ የሚመጣ፡- ኮንሶርሺያ እና የማግኔት ማመልከቻ ማስታወቂያ ደብዳቤዎች**

የNortheast ኮንሰርሺየም (James Hubert Blake፣ Paint Branch እና Springbrook 2ኛደረጃ ት/ቤቶች) እና የDowncounty ኮንሰርሺየም (Montgomery Blair፣ Albert Einstein፣ John F. Kennedy፣ Northwood እና Wheaton 2ኛደረጃ ት/ቤቶች) የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ወላጆች በውሩ መጨረሻ ለ2014–2015 የትምህርት አመት የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ምደባ ደብዳቤዎች ይቀበላሉ።

ደብዳቤው በሁሉም ኮንሶርሽያ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ስለ ምዝገባ ስብሰባዎች ዝርዝሮች ያካትታል። የDowncounty ኮንሶርሺየም እና Blake እና Springbrook 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የምዝገባ ስብሰባዎች የሚከናወኑት ረቡእ፣ ፌብሩ. 5 በ7 p.m. ነው። የPaint Branch High School ስብሰባ የተመደበው ሀሙስ፣ ፌብሩ. 6 በ7 p.m. ነው። የሁሉም ስብሰባዎች የበረዶ ቀን ማክሰኞ፣ ፌብሩ. 11 ነው።

በተጨማሪ፣ ለመካከለኛ ደረጃ ማግኔት ኮንሶርሺየም ያመለከቱ የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ወላጆች በፌብሩወሪ መጀመርያ ላይ የማስታወቂያ ደብዳቤዎች በፖስታ ይቀበላሉ። ለ2ኛ ደረጃ ት/ቤት የማግኔት ፕሮግራም ያመለከቱ የአምስተኛና የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ወላጆችም በፌብሩወሪ መጀመርያ ላይ የማስታወቂያ ደብዳቤዎች በፖስታ ይቀበላሉ ለ2ኛ ደረጃ ት/ቤት የማግኔት ፕሮግራሞች Roberto Clemente፣ Eastern እና Takoma Park የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች እና Montgomery Blair፣ Poolesville፣ Richard Montgomery እና Wheaton 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ያካትታሉ።

ኮንሶርሽያ እና የማግኔት ፕሮግራሞች

**የላቀ የት/ቤት መሪ ለሽልማት ሰይሙ።**

በዚህ አመት የት/ቤት መሪዎች እውቅና ለማግኘት ብዙ እድሎች አሉ። በአላማ ፅናታቸውና ቆራጥነታቸው እውቅና እንዲያገኙ፣ ርእሰመምህርን፡ አማካሪን ወይም SGA (የተማሪ አመራር ማህበር) ለመሰየም አስቡበት። ሁሉም ሽልማቶች ለማመልከቻዎች ማስገቢያ የጠበቀ የግዜ ገደብ አላቸው። ዝርዝር መርጃዎች ለማግኘትና ማመልከቻዎች ለማውረድ/ለማግኘት፣ ለመካከለኛ ደረጃ ሽልማቶች እዚህ እና ለ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ደግሞ እዚህ ጠቅ ያድርጉ።

ተጨማሪ መረጃዎች ያስፈልግዎታል? ኢሜይል Karen_L_Crawford@mcpsmd.org።

**እንዲሁም...**

**ለትምህርት ቦርድ የተማሪ አባል እጩዎች ለማቅረብ የሚፈልጉት ጥያቄ አለ ወይ?**

እድልዎ አሁን ነው! የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ለ2014-2015 የትምህርት አመት እጩዎች ጥያቄ እንዲያቀርቡ ተጋብዘዋል። ጥያቄዎቻችሁን በኢሜይል ለmcpssec@gmail.com ላኩ። ስማችሁን፣ ት/ቤታችሁን፣ ክፍላችሁን እና ጥያቄአችሁን ማካተታችሁን አረጋግጡ። የተወሰኑ ጥያቄዎች ለ*Meet the Candidates* (እጩዎቹን ተገናኙ) ለሚባለው የቴለቪዥን ትርእይት ይመረጣሉ። ጥያቄአችሁን የምታቀርቡበት የጊዜ ገደብ 4p.m. አርብ፣ ፌብሩ. 21 ነው።

**የትምህርት ቦርድ አዳዲስ ሹማምንት ይመርጣል**

ሀሙስ፣ ዲሴም. 12 Philip Kauffman (ፊሊፕ ካውፍማን) የትምህርት ቦርድ ፕሬዚዴንት ሆኖ እንዲያገለግል በሥራ ባልደረቦቹ ተመርጧል። Patricia O'Neill (ፓትሪሺያ ኦ'ኔይል)ም ምክትል ፕሬዚደንት ሆና ተመርጣለች። ሁለቱም ሹማምንት ለአንድ አመት ያገለግላሉ። Mr. Kauffman የሚተኩት ባለፈው አመት በፕሬዚደንትነት ያገለገሉትን Christopher S. Barclayን ነው።

Mr. Kauffman ወደ ትምህርት ቦርድ መጀመርያ የተመረጡት በ2008 ሲሆን በ2012 እንደገና በመመረጥ ሁለተኛ የአራት አመት ጊዜአቸውን እያገለገሉ ነው። ባለፈው አመት፣ የቦርዱ የፋይናንስ አስተዳደር ኮሚቴ ሊቀ መንበር እና (a member of the Committee on Special Populations) የልዩ ህዝቦች ኮሚቴ አባል ሆነው አገልግለዋል።

የኦንሌይ (Olney) ነዋሪ የሆኑት Mr. Kauffman የአካባቢና የካውንቲ PTA ተመራጭ መሪ በመሆን የተለያዩ ሚናዎች በመጫወት 13 አመቶች አገልግለዋል። Montgomery County Council of Parent-Teacher Associations (በMontgomery County የወላጅ-አስተማሪ ማህበራት)(MCCPTA) Board of Directors (የዳይሬክተሮች ቦርድ) ለሼርዉድ ክላስተርና ኖርትኢስት ኮንሶርሺየም ያካባቢ ምክትል ፕሬዚደንት ሆኖ አገልግሏል። የMCCPTA Blake ክላስተር አስተባባሪ እና የFarquhar መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት PTA ፕሬዚደንት ነበሩ። በሜይ 2007፣ የሜሪላንድ PTA Honorary Life Membership (ሙሉ የህይወት አባልነት) ተሸልሟል።

QuickNotes mcps

ወሮ/ O'Neill፣ የቤተስዳ ተቀማጭ፣ ወደ ትምህርት ቦርድ የተመረጠችው በ1998 ሲሆን በቦርዱ ከሁሉም ለበለጠ ጊዜ ያገለገለች ናት። የቦርዱ ፕሬዚደንትና ምክትል ፕሬዚደንት በመሆን በያንዳንዱ አራት ጊዜ አገልግላለች። ባለፈው አመት፣ የቦርዱ የመመርያ (Policy) አስተዳደር ኮሚቴ እና የስልታዊ ፕላን ኮሚቴ(Strategic Planning Committee) አባል ሆና ነበር።

**አትርሱ!**

Superintendent Joshua Starr በዲሴም. 10 ለትምህርት ቦርድ የ $2.23 ቢሊዮን የ2015 የስራ ማስኬጃ በጀት ረቂቅ አቅርቧል። በቀረበው በጀት ያለዎትን ሀሳቦችና አስተያየቶች በሚመጡት ሁለት ስብሰባዎች ማጋራት ይችላሉ፡ የመጀምርያው ህሙስ ጃንዩ. 9 በ7 p.m. ነው፤ ሁለተኛው ሀሙስ ጃንዩ. 16 በ7 p.m. ነው። ሁለቱም ስብሰባዎች በCarver Educational Services Center, 850 Hungerford Drive in Rockville አዳራሽ ይከናወናሉ። ከስብሰባዎቹ ባንዱ ለመናገር ከሰኞ ዲሴም. 16 ጀምሮ መመዝገብ ይችላሉ።

ቦርዱ በተጨማሪ ማክሰኞ ጃንዩ. 21 እና ሀሙስ ጃንዩ. 23 ሁለት የበጀት ስራ ስብሰባዎችን ይመራል። እነዚህ ስብሰባዎች ለህዝብ ክፍት ናቸው። ማክሰኞ ፌብሩ. 11፣ ቦርዱ ለካውንቲው ስራ አመራርና ለካውንቲው ምክር ቤት ለግንዛቤ የሚቀርብ በጀት እንዲያፀድቅ ይጠበቃል።

**እንዲሁም...**

***ጎርቤት ለጎረቤት***

የጎረቤት ለጎረቤት (N2N) ዘመቻ በመካሄድ ላይ ነው። ስለ MCPS የስራ ማስኬጃ በጀትና የደወል ሰአቶች በN2N ውይይቶች የመሳተፍ እድል አሁንም አላችሁ። ለተጨማሪ መረጃ የጎረቤት ለጎረቤት ድረ ገብያ ይጎብኙ።